# የመምህር ኤስድሮስ የሕይወት ታሪክና አበርክቷቸው

አሻግሬ አምጤ*

Abstract

This article presents the ups and downs of mämmhïr Esdros went through in his pursuit for knowledge and research. It presents the life history of mämhər Esdros from childhood up to death and his education and teachings which earned him the title "arat ayna" which literally means four- eyed referring to his excellence in the four branches of the EOTC education. Data used to write about the history of the scholar were collected from chronicles and secondary sources. The analysis shows the scholar's contribution, struggle and religious perseverance. Attempt has been exerted and care was taken to read and cross check, in as much as possible, all the available sources regarding the scholar so that there would be no mismatches of time, place, and actions regarding the scholar. As a result, I have a strong conviction that the article will promote the scholar and his historical contributions. Besides, the article will be a reason to understand the meaning of the "tač bet tərgʷame" which translates as "lower house interpretation" established by mämhər Esdros and his disciples. In his quest for research, the scholar closed his school and went to Tana Kirkos in Lake Tana (island) and read more than three hundred books, expanding his horizons of knowledge, and developed a method of interpretation called the lower house interpretation or "Yätač bet tərgʷame", which is known for its conciseness. His interpretations are presented by the phrase "Scholar Esdros has said so," in the commentaries whenever a different and additional interpretation he has taught has been included.

*ዲ.ን. አሻግሬ አምጤ በፎክሎርና ሥነ ጽሑፍ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሲኾኑ በማኅበረ ቅዱሳን የሐመር መጽሔት ዋና አዘጋጅ ናቸው።

## ፩. መግቢያ

የአራቱም ጉባኤ ቤቶች የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን የሚናገሩትና በየትርጓሜው ሐር ተጠቅሶ የሚገኘው ሐተታ መምህር ኤስድሮስ ከነገረ ሃይማኖት በተጨማሪ በታሪክ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በማኅበረሰብ እና በባህል የጥናት መስኮች መሠረት የጣሉ ሊቅ መኾናቸውን የሚያስገነዝብ ነው። ይህ ጥናት የተደረገውም ይህ የመምህር ኤስድሮስ አስተዋጽኦ ተዳፍኖ እንዳይቀር በማሰብ የሕይወት ታሪካቸውን እና አበርክቷቸውን ለማስተዋወቅ ነው። በዚህ ሥራ ሊቁን በተመለከተ በልዩ ልዩ መዛግብት ተጽፈው ከዘመናችን የደረሱ መረጃዎችን በመሰብሰብ በጊዜ ቅደም ተከተል ለመተንተን፣ የተዛነፈ ጉዳይ ሲገጥምም ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከድርጊት እና ከሌሎች ጉዳዮች አንጻር ለመመርመር እና ኹነቶችን በማገጣጠም ለማስተካከል ተሞክሯል። ይህ ጥናት ምሁራን የሌሎች ሊቃውንትን ታሪክና አበርክቶዎች እንዲያጠኑ ሊያነሣሣ ይችላል ብዬ አምናለሁ።

መምህር ኤስድሮስ እንዴት "የታች ቤት" ትርጓሜን ሊያስተዋውቁት ቻሉ? የአራቱን መጻሕፍት ጉባኤ ቤት ትርጓሜ ተምረው ሲያጠናቅቁ ወንበር ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ በኋላ ወንበራቸውን አጥፈው ብዙ መጻሕፍት ወደ ነበሩባቸው ወደ ጣና ቂርቆስ እና ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳማት እንዲሔዱ የቀሰቀሳቸው ምክንያት ምንድን ነው? የሕይወት ታሪክና አበርክቷቸው በሚገባ ሳይጻፍ የቀረበት ምክንያትስ ምንድን ነው? የሚሉት ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥናቄዎች ናቸው።

## ፪. የመምህር ኤስድሮስ የሕይወት ታሪክ

አራት ዓይና የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መኾናቸውን እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንኾን ኮውሊን (፲፱፻፸፬) እና ብሉንዴልን (፲፱፻፳፪) የመሳሰሉ የውጭ ሀገር ጸሐፍት ጭምር የመሰከሩላቸው መምህር ኤስድሮስ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይኾን ለሀገራችንም ያበረከቱትን ሁለንተናዊ ዕውቀት ከማቅረቤ አስቀድሞ አስተዳደጋቸውን በማስተዋወቅ እጀምራለሁ።

### ፪.፩.ትውልድና አስተዳደግ

መምህር ኤስድሮስ የተወለዱበትን ዘመን እና የወላጆቻቸውን ስም የሚገልጥ መረጃ ለጊዜው አልተገኘም (ዳንኤል፣ ፳፻፲፪፣ ገጽ ፬፻፵፮)። መምህር ኤስድሮስ በዐፄ ኢዮአስ ዘመነ መንግሥት በጎንደር ይኖሩ እንደ ነበረ የንጉሡ ዜና መዋዕል ቢገልጥም ሊቁ ከመቼ ጀምሮ በጎንደር መኖር እንደ ጀመሩ በትክክል አይታወቅም። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፳፬) "ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ትርጓሜ ስልት እና ምርምር የሚጠቀሱት፣ የዕውቀት በር የከፈቱት መምህር ኤስድሮስ በትግራይ ክፍለ ሀገር በተንቤን አውራጃ በ፲፰ኛው ምዕት ተወለዱ” በማለት ቢጽፉም ሊቁ ሊወለዱ የሚችሉት በ፲፯ኛው ምእት መጨረሻ አጋማሽ አካባቢ ሊኾን ይችላል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ለዚህ ግምቴ እማኝ አድርጌ የማቀርበው መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ሊቁ መምህር ኤስድሮስ “የታች ቤት ትርጓሜን” ያዘጋጁት በ፲፯፻፲፮ ዓ.ም. መኾኑን መግለጣቸውን ነው (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/፣ ፳፻)፡፡ ሊቀ ሊቃውንት መንክር መኮንን (፳፻፲፬፣ ገጽ ፭) “የመጻሕፍት ትርጓሜ የተወሰነው በ፲፯፻፲፮ ዓ.ም. በነገሡት በዐፄ ዮስጦስ ዘመነ መንግሥት በተነሡት በመምህር ኤስድሮስ ትጋት እንደ ኾነ ሊቃውንቱ ይናገራሉ” በማለት የጻፉትም ከመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ አሳብ ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መጻሕፍትን የተማሩት የመልክአ ኢየሱስ ደራሲ ከነበሩትና በ፲፮፻፺፩ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩት ከአባ ስብሓት ለአብ ነው (ሥርግው፣፲፱፻፸፫፣ ቅጽ ፫፣ ገጽ ፻፳)፡፡ በአጠቃላይ በ፲፯፻፲፮ ዓ.ም. አካባቢ የታች ቤት ትርጓሜን ያዘጋጁትን ሊቅ በ፲፰ኛው ምዕት ተወለዱ ማለት አሳማኝ አይደለም፡፡

የሊቁ የትውልድ አካባቢ ትግራይ መኾኑን አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማም ከሥርግው ሐብለ ሥላሴ በተመሳሳይ “የመምህር ኤስድሮስ የትውልድ አካባቢ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ተንቤን አውራጃ ነው” በማለት ገልጠዋል (ተሰማ፣፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፲፱-፳)፡፡ መልአከ ምክር ከፍያለው መራሔም እንደዚሁ የሊቁ የትውልድ አካባቢ ትግራይ መኾኑን ያስረዳሉ (ከፍያለው፣ ፳፻፫፣ ገጽ ፳፪)፡፡ በሌሎች ምንጮች ተጨማሪ ማረጋገጫ ባላገኝም የእስቴ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሕንጻ ዕድሳት ኮሚቴ ባሳተመው መጽሔት (ገጽ ፭) ብፁዕ አቡነ እንድርያስ ስለ ሊቁ መምህር ስለ መምህር ኤስድሮስ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> በሀገረ ስብከቴ ያሳደሳችሁት ታላቁ ደብረ ሃይማኖት መካነ ኢየሱስ ደግሞ እጅግ ለመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መመኪያ ከኾኑት ታሪካዊ እና ነቅዐ ሊቃውንት ከኾኑት ቦታዎች ውስጥ አንዱና ዋናው ነው፡፡ ለሁሉም በታወቀው ታሪኩ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ቤት፣ የቅኔ እና የዜማ አብያተ ጉባኤያት የነበሩበት እና አሁንም ያሉበት ብዙ ሊቃውንትንና ሊቃነ ጳጳሳትንም ያፈራ ከመኾኑም በላይ ታላቁ የታች ቤት ትርጓሜ መሥራች የኾኑት መምህር ኤስድሮስም የተማሩበትና ያስተማሩበት ቦታ ነው፡፡ ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ጣና ገብተው መጻሕፍትን መርምረው ጎንደር ወጥተው ልደታ ላይ የታች ቤት ትርጓሜን ከማስተማራቸው በፊት ትምህርታቸው(የተማሩት) መካነ ኢየሱስ ከአለቃ ዕንቍ ሥላሴ ከመኾኑም በላይ እርሳቸውን ተክተው ወንበር ዘርግተው ያስተማሩበት ቦታ ነው፡፡

መምህር ኤስድሮስ የተወለዱበት ቦታም ከዚሁ ከመካነ ኢየሱስ በስተደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በእግር የሁለት ሰዓት መንገድ እንደ ተጓዙ በሚገኘው በአጋጥ ኢየሱስ ደብር ነው። የእናታቸውም ቦታ ከዚያው አጥቢያ ድንበርተኛ የኾነው አራጥ ሩፋኤል ነው። ጎንደር ታች ቤቱንም ሲያስተምሩ ከኖሩ በኋላ ተመልሰው መጥተው ያረፉት እዚሁ መካነ ኢየሱስ ነው” ብለዋል።

የብፁዕነታቸው ጽሑፍ ስለ ሊቁ (ስለ መምህር ኤስድሮስ) ብዙ መመርመር ያለብን ጉዳይ መኖሩን የሚያስገነዝብ ነው። የብፁዕነታቸውን አሳብ የሚያጠናክር ተጨማሪ መረጃ አላገኘሁም። ልዩ ልዩ የታሪክ ምንጮች የሚገልጡት የሊቁ የትውልድ ቦታ ትግራይ መኾኑን ነው። መምህር ኤስድሮስ በተወለዱ ጊዜ የዓይናቸው ብርሃን ተሟልቶ የተወለዱ ቢኾንም ብርሃናቸውን ያጡት ከተወለዱ ከሦሳሳ ቀናት በኋላ በአካባቢው በተከሠተ የፈንጣጣ በሽታ ነበር። ኤስድሮስ ዐሥራ አንድ ዓመት ሲኾናቸው አባ ሐደራ ከተባለ ገዳም ገብተው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጀመሩ። በዚያው ገዳም ፊደል ቈጥረው ዳዊት ከደገሙ በኋላ ጾዋትወ ዜማ እና አቋቋም በሚገባ ተምረው አጠናቀቁ (ሥርግው፣ ፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፳፭)።

ሊቁ ቅኔ በሚገባ ተምረው ለማወቅ ብቻ ሳይኾን ወንበር ዘርግተው ለማስተማር የሚያስችል ዕውቀት ገብይተው የተመረቁት በአክሱም ጽዮን (ሥርግው፣ ፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፳፩) ሲኾን ትርጓሜ መጻሕፍትን የተማሩት ደግሞ ጎንደር ነው (ዳንኤል፣ ፳፻፲፪፣ ገጽ ፩፻፵፯)። ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መጻሕፍትን ጎንደር ከተማ ከነበሩ መምህራን መማራቸውን፣ መጻሕፍተ ብሉያትን ከአባ ስብሐት ለአብ፣ መጻሕፍተ ሐዲሳትን ከአለቃ ኃንጉል፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትን ከእጨጌ ሄኖክ፣ መጻሕፍተ መነኰሳትን ከመምህር ሙሴ ተምረዋል በማለት አምሳሉ ተፈራ (፳፻፲፩፣ ገጽ ፸፯) ገልጠዋል። እኔም ካገኘኋቸው መረጃዎች በመነሣት መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መጻሕፍትን የተማሩት ጎንደር ነው እላለሁ። ለዚህ አቋሜ ተጨማሪ እማኝ የማደርገው ሊቁን ትርጓሜ መጻሕፍት ያስተማሯቸው ሊቃውንት በሙሉ ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ የኖሩት ጎንደር የነበረ መኾኑን ነው። ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መጻሕፍትን የተማሩት ጎንደር ከተማ ነው ከሚለው አቋም ላይ እንድደርስ ያደረገኝ ሌላው ምክንያት ደግሞ በዘመኑ ጎንደር የአገራችን ርእሰ ከተማ ስለ ነበረችና ብዙ ሊቃውንትም ተሰብስበውባት ስለ ነበረ መምህር ኤስድሮስም የሊቃውንት ማእከል ወደ ነበረችው ወደ ጎንደር ሄደው ተምረዋል የሚለው እሳቤ ስላሳመነኝ ነው።

መምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መጻሕፍትን ጎንደር መማራቸውን የሚያስረግጥልን ሌላው ማስረጃ አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ (፲፱፻፹፫) እና ቴዎድሮስ አብርሃ (ኢ. አ፣ ቅጽ ፪፣ ገጽ ፩፻፸፩) ከእጨጌ ቃለ ዐዋዲ መማራቸውን፣ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ

(፲፱፻፷፪) እና ካውሊ (፲፱፻፸፬) እንደሚሉት ደግሞ ከመምህር ጓንጕል መማራቸውን መግለጣቸው ነው፡፡ እዚህ ላይ መረዳት የሚያስፈልገው እጨጌ ቃለ ዐዋዲ በጎንደር ዘመነ መንግሥት የአዘዞ ተክለ ሃይማኖት እጨጌ የነበሩ ቢኾንም መምህር ኤስድሮስ ከእርሳቸው አለመማራቸውን ነው፡፡ አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ (፲፱፻፺፫፣ ገጽ ፲፪-፲፬) እንደሚሉት መምህር ኤስድሮስ መጻሕፍተ ብሉያትን ለጌታ ገላውዴዎስ፣ መጻሐፍተ ሐዲሳትን ለሥነ ክርስቶስ አስተምረዋል፡፡

## ፫. አራት ዓይናው ሊቅ መምህር ኤስድሮስ

አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ (፲፱፻፺፯) እና ቴድሮስ አብርሃ (፳፻፫ እ.ኤ.አ፣ ገጽ ፬፻፸፫) እንደሚሉት መምህር ኤስድሮስ ከእጨጌ ቃለ ዐዋዲ ትርጓሜ መጻሕፍትን ተምረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ትክክል አይመስልም፡፡ ምክንያቱም መረጃዎች የሚጠቁሙት መምህር ኤስድሮስ የእጨጌ ቃለ ዐዋዲ ተማሪ ከነበሩት ከአባ ስብሐት ለአብ እንጂ ከእጨጌ ቃለ ዐዋዲ አለመማራቸውን ነው፡፡ ቴዎድሮስ አብርሃ በኢንሳይክሎፒዲያ ኢትዮፒካ መምህር ኤስድሮስ መጻሕፍተ ብሉያትን ከእጨጌ ቃለ ዐዋዲ መማራቸውን ቢጽፉም መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ፣ ፳፻፣ ገጽ ፻፹፱)፣ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (፲፱፻፷፪)፣ ቀሲስ አምሳሉ ተፈራ (፳፻፲፩)፣ እና መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁንን (፳፻፱፣ ገጽ ፪፻፶-፪፻፶፩) የመሳሰሉ ሊቃውንት የሊቁ መምህር የነበሩት የእጨጌ ጓንጕል ተማሪ የነበሩት አባ ስብሐት ለአብ እንደ ነበሩ ጽፈዋል፡፡ መምህር ኤስድሮስ ከአባ ስብሓት ለአብ ዘንድ የተማሩትም ጎንደር ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ቴዎድሮስ አብርሃ እንደሚሉትም "መምህር ኤስድሮስ ዓይነ ስውር ቢኾኑም አራት ዓይና የሚል ቅጽል ስም የወጣላቸው በጎንደር ከተማ ታዋቂ ከነበሩት የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት መካከል አራቱንም ጉባኤያት ጠንቅቀው የተማሩ ቀዳሚው ሊቅ በመኾናቸው ነው" (ኢአ፣ቅጽ፪፣ገጽ ፬፻፸፫)፡፡

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ እንደሚሉት "አራቱንም ጉባኤያት ተምረው በማጠናቀቅ 'አራት ዓይና' የተባለው የመዓረግ ቅጽል የወጣላቸው የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መምህር ኤስድሮስ ናቸው፡፡ ሊቁ ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ የኖሩት ቅኔ እና ትርጓሜ መጻሕፍት ሲኾን በጉባኤያቸውም ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይኾኑ መነኵሳት እና የደብር አለቆችም ጠይቀው ለመረዳት ይገኙ ነበር" (ሥርግው፣፲፱፻፹፩)፡፡ አራቱንም ጉባኤ ጠንቅቀው በመማር ወንበር ዘርግተው በጎንደር ከተማ በማስተማራቸው ብቻ ሳይኾን ተመራማሪ በመኾናቸው፣ የጎደለውን በመሙላታቸው፣ የጠመመውን በማቃናታቸው፣ ሳይብራራ የቆየውን በማብራራታቸው፣ ብዙ ትርጓሜዎችንም በማስተካከላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ዓይና የሚል ቅጽል የወጣላቸው እና ስያሜው የተሰጣቸውም

በተማሩት የጉባኤ ዕውቀት ብቻ ሳይወሰኑ ተጨማሪ ዕውቀት ለማግኘት ጥልቅ ምርምር በማድረጋቸው ጭምር መኾኑን ካውሊ (፲፱፻፸፬፣ ገጽ ፻፳፬-፻፳፰) ገልጧል።

ሊቁ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ሁሉ አጥጋቢ መልስ በመስጠታቸው ብቻ ሳይኾን በንግግር ለዛቸው የሚወደዱ ነበሩ። ይህን ለማስረዳት ከበርካታ ጥበባዊ ንግግሮቻቸው መካከል አንዱን እንመልከት። አንድ ከሮም የመጣ ሰው የእግዚአብሔር ፊቱ ወደ የት ነው ብሎ መምህር ኤስድሮስን ይጠይቃቸዋል። እርሳቸውም መብራት አስበርተው የዚህ መብራት ፊቱ ወደ የት ነው ብለው መልሰው ሲጠይቁት የመብራቱ ፊት በአራቱም አቅጣጫ መኾኑን መለሰላቸው። እርሳቸውም መልሰው የእግዚአብሔርም ፊቱ በሁሉም አቅጣጫ ነው (ሥርግው፣ ፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፳፮) በማለት በጥበብ የመለሱለት መኾኑ ይነገራል[1]። መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ እንደሚሉት ከብዙ መምህራን የተማሩት አራት ዓይናው ሊቅ መምህር ኤስድሮስ የታች ቤት አንድምታ ትርጓሜን ያዘጋጁት በ፲፯፻፲፮ ዓ. ም ነው (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/፣ ፳፻፣ ገጽ ፻፺፬)። ይህ ዘመን ሊቁ ከተጠቀሱት መምህራን አራቱን ጉባኤ ተምረው በመምህርነት ተመርቀው ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ ማስተማሩን ትተው ጣና ደሴት ገብተው ፹፩ መጻሕፍት አስነብበው ዐዲሱን ትርጓሜ ያዘጋጁበት ነበር።

## ፬. ዐዲስ ምዕራፍ የከፈቱ ሊቅ

መምህር ኤስድሮስ ከተለያዩ ሊቃውንት ትርጓሜ መጻሕፍትን "የላይ ቤት ትርጓሜ" ተምረው በተራቸው ወንበር ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ በኋላ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ለማንበብ እና ለመመራመር ፈልገው ጉባኤያቸውን አጥፈው ወደ ጣና ገዳማት ገብተው መጻሕፍትን ማስነበብ ጀመሩ። ጉባኤያቸውን አጥፈው ጣና ሐይቅ ከሚገኙ ገዳማት አንዱ ወደ ኾነው ወደ ዳጋ እስጢፋኖስ በመሄድ ፹፩ መጻሕፍት አስነብበው ዐዲሱን ትርጓሜ አዘጋጁ። ከዚያም ያልተማርነው ምሥጢር ስላለ መጥታችሁ እየመረመርን ዕውቀታችንን እናደላድል በማለት አስቀድመው መርቀው አሰናብተዋቸው ወደ ነበሩት ደቀ መዝሙሮቻቸው ላኩ። የምላችሁን ተቀበሉኝ ሳይሉ ምሥጢር እናደላድል በማለት ወደ ደቀ መዝሙሮቻቸው መላካቸው ትሕትናቸውን የሚገልጥ ነው። ሊቁ መጻሕፍትን መርምረው ምሥጢር ያደላደሉ፣ ተመራማሪነታቸውን ሁል ጊዜ መጻሕፍትን

[1] የዚህ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም ለእጨጌ በትረ ጊዮርጊስም ከአይሁድ እና ከካቶሊካውያን ቀርበውላቸው እንደ ነበረ መጻሕፍት ያስረዳሉ። ይህም በአንድ በኩል ለአንዱ የተነገረው ለሌላው እየተጠቀሰ ሊኾን እንደሚችል ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ ካቶሊካውያን ያወቁ ሲመስላቸው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትን በዕውቀት የሚገዳደሩ የሚመስላቸው እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊኾን ይችላል። እነርሱ ሲጠይቁት የኖሩት እና ሊቃውንቶቻችን ሲመልሱላቸው የኖሩት የማይገባቸው ለዚህ ነው። የማይገባቸውን ጠይቀው ዕድሜ ልካቸውን ሲወዝግበሩ የሚኖሩበትን መልስ ተቀብለው ሄደው ራሳቸው በተረዱበት መንገድ እየጻፉ እንዲህ ብለው መለሱልን በማለት ሌሎችንም ሲያሳስቱ ኖረዋል።

በማስነበብ የገለጡ፣ የዕውቀት ክፍተታቸውን አንብበው በሚያገኙት ዕውቀት ሲሞሉ የኖሩ መኾናቸው የተመሰከረላቸው በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ብቻ ሳይኾን ሮጀርስ ካውሊን በመሳሰሉ የውጭ አገር ተመራማሪዎች ጭምር ነው። ካውሊ (፲፱፻፸፬፣ ገጽ ፻፳፬-፻፳፯) ሊቁን "አራቱንም ጉባኤያት ጠንቅቀው በመማር ወንበር ዘርግተው በጎንደር ከተማ በማስተማራቸው ብቻ ሳይኾን ተመራማሪ በመኾናቸው፣ የጎደለውን በመሙላታቸው፣ የጠመመውን በማቃናታቸው፣ ሳይብራራ የቆየውን በማብራራታቸው፣ ብዙ ትርጓሜዎችንም በማስተካከላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ አራት ዓይና የሚል ቅጽል የወጣላቸው እና ስያሜው የተሰጣቸውም በተማሩት የጉባኤ ዕውቀት ብቻ ሳይወሰኑ ተጨማሪ ዕውቀት ለማግኘት ጥልቅ ምርምር በማድረጋቸው ጭምር ነው" በማለት ገልጢቸዋል።

የመጻሕፍተ ብሉያትን፣ የመጻሕፍተ ሐዲሳትን እና የመጻሕፍተ ሊቃውንትን ምሥጢር በሚገባ አደላድለው የቀድሞውን የትርጓሜ ስልት ለተማሪዎች እንዲመች አድርገው በማቅረብ በመጻሕፍት ትርጓሜ ዐዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል። ብዙ መጻሕፍትን በማንበብ የቀድሞውን ትርጓሜ በማደሳቸው፣ ብዙ ትርጓሜም በማቃናታቸው ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ የመምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ እየተባለ ይነገራል። የሊቅነት መለኪያው መማር ብቻ ሳይኾን መመርመር ጭምር መኾኑ ግልጽ ነው። ሁል ጊዜ መጻሕፍትን ማንበብ እና መመራመር የዕውቀትንም፣ የእምነትንም ክፍተት ከመሙላት በተጨማሪ በየዘመኑ ለሚነሡ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠትም ይጠቅማል። መምህር ኤስድሮስ እጅግ በርካታ መጻሕፍትን በመመርመር የጎደለውን በመሙላት፣ ያልተመሰጠረውን በማመስጠር ለተከታዮቻቸው ያስተላለፉ፣ ዐዳዲስ ነገሮች በመጨመር ለሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ጥለው ያለፉ ሊቅ ነበሩ።

ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ወደ ደቀ መዝሙሮቻቸው "ኑ መጻሕፍትን እየመረመርን ዕውቀታችንን እናደላድል" በማለት የላኩት ጎንደር ከተማ በምትገኘው ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው፣ ጉባኤ ተክለው ለማስተማር በማሰብ ነበር። በመልእክታቸው መሠረት ብዙዎቹ ደቀ መዝሙሮቻቸው ወንበር ዘርግተው ከሚያስተምሩበት ጉባኤያቸውን አጥፈው፣ ጥሪያቸውን አክብረው፣ ወደ መምህራቸው በመሄድ "የታች ቤት ትርጓሜ" የሚባለውን ዐዲሱን የትርጓሜ ስልት ተምረዋል። ሊቁ የታች ቤት የሚባለውን ትርጓሜ ካዘጋጁ በኋላም የላይ ቤት ትርጓሜን ፈጽመው ሳይተው ለዐዲሱ ትርጓሜ የሚኾነውን እየመረጡ በመውሰድ ይጠቀሙበት እንደ ነበረ ይነገራል (ሥርግው፣፲፱፻፹፩)። የመምህራቸውን መልእክት ሳይቀበሉ የቀሩት ደግሞ የጥንቱን ይዘው በመቀጠላቸው ምክንያት ትርጓሜያቸው "የላይ ቤት ትርጓሜ" ተብሏል።

የመምህር ኤስድሮስን መልእክት ሰምተው በመምጣት ዐዲሱን ትርጓሜ የተማሩት ደቀ መዝሙሮቻቸው ብዙ ቢኾኑም ጌታ ዮናስ የተባሉ ደቀ መዝሙራቸውና ሌሎችም "ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት፤ እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም" በማለት ወደ መምህራቸው ተመልሰው ሳይሄዱ የቀሩት መምህር ኤስድሮስ በምርምር የደረሱበትን ዕውቀት ለመቀበል ስላልፈለጉ ነው (ዐምደ ጽዮን፣ ፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፳):: በዚህ መሠረት ዐዲሱ የታች ቤት ትርጓሜ በመምህር ኤስድሮስ ከመዘጋጀቱ አስቀድሞ የተማሩትን (አንተ መምህራችን ልዩ የትርጓሜ ሐተታ ከመጨመርህ በፊት ያስተማርከን የጥንቱ የላይ ቤት ትርጓሜ) ይበቃናል በማለት በመምህራቸው የተሻሻለውን የታች ቤት አንድምታ ትርጓሜ ሳይቀበሉ ቀርተዋል:: በዚህ ምክንያት በመምህር ኤስድሮስ የተሻሻለው ዐዲሱ ትርጓሜ "የታች ቤት ትርጓሜ" ሲባል በጌታ ዮናስ እና መሰሎቻቸው የቀጠለው ጥንታዊው ትርጓሜ "የላይ ቤት ትርጓሜ" እየተባለ መጠራት ጀመረ::

"የታች ቤት ትርጓሜ" የሚባለው በመምህር ኤስድሮስ እና የመምህራቸውን ጥሪ ተቀብለው፣ ወንበራቸውን አጥፈው ወደ ትምህርት በተመለሱ ተማሪዎቻቸው ቢዘጋጅም በየዘመናቱ በተነሡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን መዳበሩ ይነገራል:: ከመምህር ኤስድሮስ በመቀጠልም ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ብዙ ምሥጢር ጨምረውበታል:: አለቃ ወልደ አብም ፺፪ መጻሕፍትን በማንበብ እና ከዐረብኛውም በመጥቀስ ትርጓሜውን ማዳበራቸው ይነገራል (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ፣ ፳፻፣ ገጽ ፻፺፴):: ከእርሳቸው በመቀጠልም የደረስጌው ገብረ ማርያም ወንበር ዘርግተው ከማስተማር በተጨማሪ በመመራመር ለትርጓሜው ልዩ ስልት እንደ ሰጡት፣ የትግሬው ወልደ ሩፋኤልም እንዲሁ ለትርጓሜው አወራረድ ልዩ ስልት እንደ ሰጡት ይነገራል (ዐምደ ጽዮን፣ ፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፲፱):: ትምህርቱም በብዛት የሚሰጠው የመምህራቸውን ጥሪ ሰምተው ወደ ጉባኤ የተመለሱ ሊቃውንት በብዛት ይገኙበት በነበረው በጎንደር እና በአካባቢው ሲኾን "የላይ ቤት"[2] አንድምታ ትርጓሜ ደግሞ በጎጃም ሲነገር መቆየቱ የሚያመለክተው የሊቁን ዳግም ጥሪ አንቀበልም ብለው ወደ ትምህርት ቤት ሳይመለሱ የቀሩት የጎጃም ሊቃውንት መኾናቸውን ነው (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ፣ ፳፻):: ኮውሊ (፲፱፻፸፬) "የላይ ቤት ትርጓሜ" የሚገኘው በጎጃም ሲኾን ብዙ ሐተታ ይጨምራል በማለት የገለጠው የሚያመለክተውም ይህንን ነው:: መምህር ኤስድሮስ ዐዲሱን ትርጓሜ ካዘጋጁ በኋላ ካስተማሯቸው ብዙ ደቀ መዛሙርት መካከል በጣም

[2] የላይ ቤት ትርጓሜ የሚባለው ከጥንት በቅብብል እስከ መምህር ኤስድሮስ የደረሰው ሲኾን ትርጓሜው ውስብስብ፣ አንድን ታሪክ ደጋግሞ የሚያቀርብ ለመማርም በጣም ብዙ ጊዜ የሚወስድ ሲኾን የታች ቤት ትርጓሜ የሚባለው አጭርና ግልጽ ማብራሪያ ያለው በመምህር ኤስድሮስ የተጀመረው ትርጓሜ ነው:: ይህ ትርጓሜ አንድ ታሪክ ሌላ ቦታ ሲገባ ለምሳሌ ቅዳሴ ማርያም ላይ የተጠቀሰ ታሪክ ውዳሴ ማርያም ላይ ወይም ኦሪት ላይ ሲያስፈልግ እንደ ቅዳሴ ማርያም ተርክ ብሎ ፍንጭ ሰጥቶ የሚያልፍ፣ ለዘመናዊ የምንጭ አጠቃቀም የቀረበ ነው:: በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ የታች ቤት ትርጓሜ በላይ ቤት ትርጓሜ የሌለ ምሥጢር ይጨምራል:: ይህም መምህር ኤስድሮስ እንዲህ ብለው ተርጕመውታል በማለት ይገለጣል:: "ገራኅተ ሙሴ" በሚለው ርእስ ሥር የተጠቀሰውን ማንበብ ጉዳዩን ግልጥ ያደርገዋል::

የታወቁት ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ፣ ሥነ ክርስቶስ እና ጌታ ገላውዴዎስ ይጠቀሳሉ (አክሊለ ብርሃን፣ ፲፱፻፺፫)። ሥነ ክርስቶስ በበኩላቸው መምህር ወልደ አብን አስተምረዋል (ኮውሊ፣ ፲፱፻፸፬)።

ለዐዲሱ የትርጓሜ ስልት መሠረት የጣሉት መምህር ኤስድሮስ ብዙ ደክመው አጭርና ግልጽ የኾነውን ትርጓሜ መጻሕፍት ለማዘጋጀት እንደ ተሳካላቸው ቴዎድሮስ አብርሃ ይገልጣሉ። መምህር ኤስድሮስ አንድን ምሥጢር በተለየ መንገድ ሲያመሰጥሩ የኖሩ ሊቅ ስለ ነበሩ የተማሪን ልቡና ለመንፈሳዊ ምርምርና አብርሆት ይቀሰቅሱ ነበር (ዐምደ ጽዮን፣ ፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፲፱-፳)። በዚህ መልኩ ዐዲሱን ትርጓሜ ከተማሩ የሊቁ ታዋቂ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ሥነ ክርስቶስ የተባለው ሊቅ መኾኑን፣ እርሱም የሸዋውን ተወላጅ ታዋቂውን ሊቅ መምህር ወልደ አብን አስተምሯል። ከዚህ ጋራ በተያያዘ ቴዎድሮስ አብርሃ የሚያስገርም በሚል የገለጡት ጉዳይ የትርጓሜ መጻሕፍት አባት የሚለው ስያሜ ለመጻሕፍት ትርጓሜ ብዙ የደከሙት መምህር ኤስድሮስ እያሉ ዐረብኛ ቋንቋ በመናገሩና በዐረብኛ የተጻፉ መንፈሳዊ ድርሰቶችን ማንበብ በመቻሉ ብቻ ለወልደ አብ ወልደ ሚካኤል መሰጠቱን ነው። ቴዎድሮስ ይህ መደረጉ ተገቢ እንዳልኾነ በአጽንኦት ይገልጣሉ (ቴድሮስ፣ ፳፻፫ እ.ኤ.አ.፣ ገጽ ፬፻፸፫)።

## ፫. ስደት እና ውግዘት

ከዳግማዊ ኢያሱ እና ከኢዮስያስ ዜና መዋዕል ማረጋገጥ የተቻለው መምህር ኤስድሮስ እስከ መስከረም ወር ፲፯፻፶፯ ዓ.ም. ድረስ በጎንደር ከተማ ውስጥ ተጽእኗቸው ከፍተኛ የነበረ መኾኑን ነው (ጊዩዲ፣ ገጽ ፪፻-፪፻፩)። ይህም የሚታወቀው ቅብዓቶች እና ጸጎች ጥምረት ፈጥረው፣ ራስ ወልደ ልዑልን አጋዥ አድርገው መምህር ኤስድሮስን ጨምሮ ሦስት ታዋቂ የተዋሕዶ እምነት ተከታይ ሊቃውንት ከጣና ሐይቅ ምሥራቃዊ ዳርቻ ከምትገኘው ምጽራሐ ደሴት እንዲጋዙ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፯፻፶፯[3] ዓ.ም. ያስፈረዱባቸው በመኾኑ ነው (ጊዩዲ፣ ገጽ ፪፻-፪፻፩)። ካይላ ሜዳ በተባለ ቦታ በተካሄደው ጉባኤ ጊዜያዊ ኅብረት ፈጥረው የነበሩት የጸጋ እና የቅብዓት ሊቃውንት በራስ ወልደ ልዑል አጋዥነት መምህር ኤስድሮስ ጎንደር ከተማን ለቀው ወጥተው በጣና ሐይቅ ምሥራቅ ከምትገኘው ምጽራሐ ደሴት እንዲጋዙ አድርገዋል። ራስ ወልደ ልዑልም ውሳኔው በዐዋጅ እንዲጸና አድርገዋል። ይህንም ጊዩዲ በአንድ ጥራዝ ባሳተመው የብርሃን ሰገድ ኢያሱና የኢዮአስ ዜና መዋዕል ላይ ጽፎታል።

[3] ዘመኑ አንድ ቦታ ላይ ፲፯፻፶፯ ዓ.ም ሌላ ቦታ ደግሞ ፲፯፻፶፮ ዓ.ም ይላል። ሁለቱም በዜና መዋዕሉ ቢካተትም እኔ ግን አንደኛውን ተጠቅሜያለሁ። አንደኛው በዋናው ዜና መዋዕል ሌላኛው ደግሞ በግርጌ ማስታወሻው መጠቀሳቸውን ልብ ይሏል።

ዘመኑ መጠነኛ ልዩነት ቢያሳይም መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (፲፱፻፶፮) በመምህር ኤስድሮስ ላይ የተፈጸመውን ግፍ አስመልክተው "ሰኔ ፲ ቀን ፲፯፻፸፫ ዓ.ም. በዕለተ እሑድ በዘመኑ የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበረው አባ ተስፋ[4] አባ ኤስድሮስን '*ሥጋ* በተዋሕዶ ከበረ' በማለት በማመናቸው አውግዟቸዋል" በማለት ጽፈዋል። ብሉንዴል ያሳተመው *ታሪከ ነገሥት* "አመ ዐሥሩ ለሰኔ በዕለተ እሑድ ተወግዘ አባ ኤስድሮስ በቤተ እጨጌ እንዘ ይብል ከብረ *ሥጋ* በተዋሕዶ ምስለ *ቃ*ለ እግዚአብሔር ወተቀብዓ ከመ ፩ እም ቅዱሳን ወተወክፈ ቦቱ ልደተ ክብር ዘከማነ። እስመ እምቅድመዝ ይብል አባ ኤስድሮስ መንፈስ ቅዱስ ዘተዋሐደ ቦቱ ኮኖ ቅብዓተ ለ*ሥጋ*፡- በዕለተ እሑድ ሰኔ ዐሥር ቀን ፲፯፻፸፫ ዓ.ም. አባ ኤስድሮስ *ሥጋ* ከአካላዊ *ቃ*ል *ጋ*ር በመዋሐዱ ከበረ። እንዲሁም ከቅዱሳን እንደ አንዱ ክብርን አገኘ በማለቱ እጨጌው በጠራው ጉባኤ ተወገዘ። ከዚያ አስቀድሞ አባ ኤስድሮስ የተዋሐደበት መንፈስ ቅዱስ የ*ሥጋ* ክብር ኾነው" በማለት ያምን እንደ ነበር ተጽፏል (ብሉንዴል፣፲፱፻፷፪፣ ገጽ ፷፯)።

*ሥርግው ሐብለ ሥላሴ* (፲፱፻፹፩) ስለ ሊቁ መምህር ኤስድሮስ "አስቀድሞ የተዋሐደበት መንፈስ ቅዱስ ለ*ሥጋ* ቅብዕ ኾነው በማለት የሚያምኑ የቅብዓት ተከታይ ነበሩ፤ በኋላ ግን ከእግዚአብሔር *ቃ*ል *ጋ*ር *ሥጋ* በተዋሕዶ ከበረ፤ የመወለድ ክብርም እንደ እኛ ተቀበለ በማለት የሚያምኑ ኾነዋል" በማለት የጻፉት የብሉንዴልን መጽሐፍ መነሻ አድርገው ይመስላል። ጽሑፉ የሊቁን ስም ለማጉደፍ የተጻፈ ሲኾን፣ መረጃ አቀባዩም በተዋሕዶ ከበረ ብለው የሚያምኑ ሊቃውንት ያላሉትን እንዳሉ፣ የማያምኑበትን እንደሚያምኑ አስመስሎ በማቅረብ የዋህንን ለማሳሳት ያስጻፈው (ከሌላ ወገን የኾነ) ይመስላል። መምህር ኤስድሮስ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ብለው የሚያምኑ ቢኾኑ ኖሮ ሦስት ልደት የጸ*ጋ* ልጅ ብለው ያምኑ በነበሩት በእጨጌ ተስፋ አይወገዙም ነበር የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም መምህር ኤስድሮስ ቅብዓት ስለ ነበሩ ተወገዙ እንዳንል አስቀድመን በጠቀስነው ኢግናስዮ ጊዩዲ ባሳተመው የአራት የጎንደር ነገሥታት ዜና መዋዕል በቅብዓት ከበረ ባዮች እና ሦስት ልደት የጸ*ጋ* ልጅ ባዮች ኅብረት ፈጥረው በተዋሕዶ ከበረ ባዮችን ሲያሳድዱ እርሳቸውም ተሳደዋል።

ሊቁ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ፣ ሦስት ልደት ወይም የጸ*ጋ* ልጅ ብለው ያምኑ የነበረ ቢኾን የጸ*ጋ* ልጅ ብለው ያምኑ በነበሩት እጨጌ አይወገዙም ነበር ብዬ አምናለሁ። የሊቁ የመምህር ኤስድሮስ ደቀ መዝሙር የኾኑት የዐ*ቃ*ቤ ሰዓት ከብቴ *ታሪክ* የተሻለ ተጽፎ ስለሚገኝ እና መምህር ኤስድሮስ ከጎንደር ሲሳደዱ የጸ*ጋ* ልጅ በማለት ያምኑ የነበሩት ዐ*ቃ*ቤ ሰዓት ከብቴ መሾም መሸለማቸው የሚጠቁመውም መምህር ኤስድሮስ የተሳደዱት በተዋሕዶ ከበረ ብለው የሚያምኑ ሊቅ በመኾናቸው እንጂ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ በማለታቸው አለመኾኑን ነው። ሊቁ የተወገዙት የንጉሡ ማዕድ ባራኪ

4 አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ በመጽሔተ አሚን ገጽ ፱፬ ተስፋ ጊዮርጊስ በማለት መዝግበውታል።

(ቄስ ዐዔ)፣ በሃይማኖት ደግሞ የጸጋ ልጅ ብለው ያምኑ የነበሩት ደቀ መዝሙራቸው ከብቴ ግንቦት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. ዐቃቤ ሰዓት ኾነው በተሾሙ በወሩ ነበር (ብሉንዴል፣ ፲፱፻፹፱፣ ገጽ ፷፫)። ይህም መምህር እና ደቀ መዝሙር በሃይማኖት በመለያየታቸው ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ መምህራቸውን ከስደትም ቢሉ ከውግዘት ለመታደግ አለመፈለጋቸውን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ዘመኑ ጸጎች የቤተ ክርስቲያንን ዋና ዋና ሓላፊነት ጠቅልለው የያዙበት፣ በአንጻሩ ደግሞ ተዋሕዶዎች ይሳደዱ የነበሩበት መኾኑንም ይጠቁማል።

## ፮. የመምህር ኤስድሮስ አበርክቶ

የመምህር ኤስድሮስ አበርክቶ በልዩ ልዩ መልክ ሊገለጥ ይችላል። በግራኝ አህመድ ወረራ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት ከተቃጠሉ፣ መጻሕፍትም ከተቆነጻጸሉ በኋላ የመጻሕፍትን ንባብ እና ትርጓሜ ማቃናታቸውን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ (ዐምደ ጽዮን፣ ፲፱፻፸፱፣ ገጽ ፹)። መምህር ኤስድሮስ አንድን ጉዳይ በጥልቀት መመርመር፣ ምሥጢር ማቃናት፣ በተለየ መንገድ ማየት፣ ድግግሞሹን ማስቀረትና ምንጩን ጠቁሞ ማለፍ ከአበርክቶዎቻቸው ጥቂቶቹ ናቸው። አቀራረባቸውም የዘመናዊ ምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። የተባለውን ከመድገም ይልቅ ምሥጢርን ከምሥጢር ማገናኘት እና ዐዲስ መንገድ ሠርቶ ማሳየት የሚታወቁ የሊቅነታቸው መገለጫዎች ናቸው። እንዲህ ያለው መንፈሳዊ ምሥጢር የሚገለጠው በዐውቀት (በትምህርት) ብቻ ሳይኾን በመንፈሳዊ ብቃትና በሱባኤ ጭምር መኾኑ ይታወቃል። ሊቁም የኖሩት በስደትና በሱባኤ በመኾኑ እንዲህ ያለውን ምሥጢር ለማፍለቅ በቅተዋል።

መምህር ኤስድሮስ በነባሩ የአንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት ላይ ምሥጢር በማስፋፋት ባደረጓቸው በርካታ አስተዋጽኦዎች ሲታወሱ ይኖራሉ። ከእነዚህ ሥራዎቻቸው መካከል በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፪÷፳፱፤ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፫÷፳፣ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ፣ ፳፻፣ ገጽ ፻፺፩) እና በሌሎችም መጻሕፍት ትርጓሜዎች የሰጧቸው ትንታኔዎች ለአብነት ይጠቀሳሉ። ሊቁ መምህር ኤስድሮስ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜም ኾነ በሌሎች መጻሕፍት ከነባሩ ትርጓሜ የጨመሩት መምህር ኤስድሮስ ደግሞ እንዲህ ብለው ተርጉመውታል እየተባለ ተገልጦ ይገኛል። ለምሳሌ፡- በማክሰኞ ውዳሴ ማርያም የምናነበው ነባሩ ትርጓሜ፡-

> አንቲ ውእቱ ገራህት ዘኢተዘርአ ውስቴታ ዘርእ፣ ለታብቊል ምድር ኵሎ ሐመልማል። ዘርእ ዘይዘራእ በበጽጌሁ፣ ወበበእንሊሁ፡- ባለ ጊዜ ገበሬ ሳይጥርባት፣ ሳይግርባት፣ ዘር ሳይወድቅባት ለምልማ፣ አብባ፣ አፍርታ የተገኘች ገራኅተ ሠሉስ [የማክሰኞ እርሻ] አንቺ ነሽ። ገራኅት የእመቤታችን

ምሳሌ ሲኾን ፍሬ የጌታ ምሳሌ ነው"። አንድም 'ገራኅተ አብርሃም አንቺ ነሽ'ይላል። 'እግዝእትየ ገራኅቱ ለአብርሃም፡-እመቤቴ የአብርሃም እርሻ አንቺ ነሽ' በማለት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በድጓው እንደ ገለጠው። በአብርሃም እርሻ በውስጥ ሰው ይቀብሩባታል፣ በውጭ ዘር ይዘሩባታል። አንድም በአተ ካዕበትነት ያላት ዕልፍኝ ካዳራሽ ናት። ሰው ሲቀብሩ የሰነበተውን ያርቁባታል፤ የዕለቱን ያቀርቡባታል። እንዲህ የሚያደርጉት ሽቱ ለመቀባት ይመቻቸው ዘንድ ነው። ለገራኅተ አብርሃም ሁለት ግብር እንዳላት ሁሉ እመቤታችንም ሁለቱን መስተጻርራን ማለትም እናትነትን ከድንግልና፣ ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራ ይዛ ተገኝታለችና በአብርሃም እርሻ ትመሰላለች። 'አንቲ ውእቱ ለአብርሃም ማኅተመ ጽድቁ፣ ገራኅት አንቲ ዘተሣየጣ በወርቁ፡- የአብርሃም የጽድቅ ማኅተሙ በወርቁ የተወዳጀሽ እርሻ አንቺ ነሽ' እንዲል እንዚራ ስብሐት። አንድም 'ገራኅተ ሙሴ' አንቺ ነሽ ይላታል። እንዲህ ማለቱ እንደ ምን ነው? ቢሉ ሙሴ ለእግዚአብሔር ከነበረው ባለሟልነት የተነሣ ጌታን ተገልጠህ ፊትህን አሳየኝ ብሎ ለምኖት ነበር። እግዚአብሔርም 'አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ ወየሐዩ አሐተ ሰዓተ፡- ሰው ፊቴን ዐይቶ አንድ ሰዓት እንኳ ጸንቶ መቆም አይቻለውም'[5] በማለት መለሰለት። ሙሴም መልሶ 'እንግዲያ ባለሟል መባሌ በምን ይታወቃል' አለው። እግዚአብሔርም እንግዲያውስ ገበሬ ካልጣረባት፣ ካልጋረባት፣ ዘር ካልወደቀባት ከድንግል እርሻ የበቀለች ስንዴ አምጥተህ ብትሠዋልኝ እገለጥልሃለሁ አለው። 'ሙሴሰ የዋህ እምኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል' ይለዋልና ለጊዜው አገኘለሁ መስሎት በራእይ ሲባክን፣ በልቡናው ሲያወጣ፣ ሲያወርድ አድሯል። ጌታ ግን እንዲህ ማለቱ በምሥጢር ነው። በኋላ ድንግል እርሻ ከተባለች ከድንግል ማርያም ተወልጄ በጠባብ ደረት፣ በአጭር ቁመት ተወስኜ፣ መሥዋዕት ኾኜ በምቀርብበት ጊዜ እገለጥልሃለሁ ሲለው ነው። ይኸውም አልቀረበትም፤ በደብረ ታቦር ተገልጦለታል የሚለው ነው።

መምህር ኤስድሮስ በነባሩ ላይ የጨመሩት ደግሞ "*ይበቅልልኛል ብሎ፣ የብረት መደብ አሠርቶ፣ ያንን አፈር ሞልቶ፣ ውኃ እያጠጣ አርባ ዘመን ይዞት ተጉዟል*" የሚል የረቀቀ ምሥጢር ነው (ደምፀ፣ ፳፻፯)። በዚሁ በማክሰኛ ውዳሴ ማርያም ነቢዩ ዳንኤል በታላቅ ተራራ ላይ ያየውን ራእይ በተመለከተ ነባሩ ትርጓሜ "ራሱ የወርቅ የተባለው ናቡከደነፆር፣ አንገቱና ደረቱ የብር የተባለው ዳርዮስ፣ ወገቡ የብረት የተባለው ቂሮስ፣ ጭንና ጭኑ የብረት የተባለው እስክንድር፣ አንድ እግሩ የሸክላ ሌላው እግሩ የብረት የተባሉት ሁለቱ ኃያላን እና ሁለቱ ድኩማን የእስክንድር ልጆች መኾናቸውን ልጅ

[5]. ዘፀ. ፴፫÷፲፱።

የለውም ቢሉ ደግሞ ሁለቱ ኃያላን ሁለቱ ድኩማን አሽከሮቹ" መኾናቸውን በሚገባ ተንትኖ ያስረዳል (ደምፀ፣ ፷፻፯)።

መምህር ኤስድሮስ ነባሩን ትርጓሜ በተለየ መንገድ የተረጎሙት "ራሱ የወርቅ፤ አንገቱና ደረቱ የብር የተባሉት በሦስቱ ዓለመ መላእክት የሚገኙ መላእክት ናቸው። ጭንና ጭኑ የብረት፣ አንድ እግሩ የሸክላ ሌላው እግሩ የብረት ምስል የተባሉት በዚህ ዓለም የሚገኙ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት እና ደቂቀ አዳም ናቸው። የሰው እጅ ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ ደንጊያ ወርዶ ቀጥቅጦ በዓለሙ ሲመላ ተመልሶ ተራራ ሲያህል ያንንም ነፋስ ጠራርጎ ሲያጠፋው ማየትህ በኋላ ዘመን ሥጋ የባሕርይ አምላክ ኾኖ ይህን ሁሉ አሳልፎ የመኖሩ ምሳሌ ነው። ደገኛ ነገር ገልጦልሃል፤ ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው" በማለት ነው (ደምፀ፣ ፷፻፯)። መምህር ኤስድሮስ በግራኝ አህመድ ወረራ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት ከተቃጠሉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ከተቆነጻጸሉ በኋላ የመጻሕፍትን ንባብም፣ ትርጓሜም አቃንተው ለመጻፍ እና ለማስተካከል ብዙ ደክመዋል በማለት ኅሩይ ወልደ ሥላሴ (፲፱፻፷፫) የገለጡትም እንዲህ ያለውን የሊቁን አበርክቶ ስለሚያውቁ ነው።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፪፣ ቊጥር ፳፮ "ወኢርአዮ መንፈስ ቅዱስ ከመ ኢይሙት ዘእንበለ ይርአይ መሲሖ ለእግዚአብሔር፦ እግዚአብሔር በተዋሕዶ ያከበረውን ወልድን ሳያይ እንዳይሞት መንፈስ ቅዱስ ነግሮት ነበር" በማለት ስምዖን አረጋዊ ጌታችን፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳያይ እንዳይሞት ማድረጉን ይነግረናል። ሐተታውንም በጥሊሞስ የሚባል መፍቀሬ ጥበብ የግሪክ ንጉሥ በዕብራይስጥ በተጻፉ መጻሕፍት ውስጥ ልዩ ልዩ ጥበብ እንደሚገኝባቸው ሲሰማ ፸፪ ሊቃውንተ አይሁድን ሰብስቦ፣ ሁለት ሁለት አድርጎ በመመደብ ሠላሳ ስድስት መጻሕፍት ሰጣቸው። በዚህ ጊዜ ለስምዖን የደረሰው ትንቢተ ኢሳይያስ ነበር። ስምዖን ትንቢተ ኢሳይያስን ሲተረጕም "ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልድን ትወልዳለች" ከሚለው አንቀጽ ሲደርስ እንኳን የአሕዛብ ንጉሥ ይቅርና ትንቢት የተነገረላቸው የእስራኤል ንጉሥስ ቢኾን ይህን አምኖ ይቀበላልን? በማለት ድንግል የሚለውን ወለት[6] ብሎ ቀየረው (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/፣ ፲፱፻፺፪)።

ወዲያውም እንቅልፍ ወስዶት ቢነቃ የጻፈው ተፍቆ ድንግል በሚለው ቃል ተተክቶ አገኘው። እንደ ገና ሰርዞ ወለት ብሎ ጻፈው። አሁንም እንቅልፍ ያዘውና ቢነቃ የጻፈው ተፍቆ ድንግል በሚለው ቃል ተተክቶ አገኘው። እንዲህ እያለ ሦስት ጊዜ ተደጋገመ። በሦስተኛው መልአከ እግዚአብሔር ተገልጦ የተጠራጠረውን ሳያይ እንደማይሞት ነገረው። ሊቃውንት በሐተታቸው ስምዖን በዚህ ምድር የኖረው ፫፻ ዘመን ነው ያሉ

[6] ወለት የሚለው የግእዝ ቃል ሲኾን ትርጕሙም ሴት ልጅ ማለት ነው።

እንደ ኾነ ትንቢተ ኢሳይያስን ሲተረጕም የ፪፻፶፪ ዓመት ሰው ነበር። ከዚያ በኋላ ደግሞ ፪፻፶ ዓመት ኖሯል። ስምዖን በዚህ ምድር የኖረው ፫፻ ዓመት ነው ያሉ እንደ ኾነ ትንቢተ ኢሳይያስን ሲተረጕም የ፻፶ ዓመት ሰው ሲኾን ከዚያ በኋላ ደግሞ ፻፶ ዓመት ኖሯል እስከሚለው ድረስ ነባሩ ትርጓሜ ነው። መምህር ኤስድሮስ የጨመሩት ወይም በተለየ መንገድ የሰጡት ሐተታ "ስምዖን ትንቢተ ኢሳይያስን ሲተረጕም የ0ሥራ ዐምስት ዓመት ብላቴና ነበር" የሚል ነው። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፩፣ ቊጥር ፲፬ ላይ ታሪኩ ተጽፎ ስለምናነበው መጻጕዕ "ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ተነሥተህ አልጋህን ተሸክመህ ሒድ" በማለት የተጻፈውን መምህር ኤስድሮስ የተረጐሙት "ጽንዐ ተአምራቱን ለማጠየቅ አልጋው የብረት አልጋ ነው" በሚል ነው።

## ፮. ስለ መምህር ኤስድሮስ የምሁራን አስተያየት

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (፲፱፻፹፩) መምህር ኤስድሮስ "አስቀድሞ የተዋሐደበት መንፈስ ቅዱስ ለሥጋ ቅብዕ ኾነው በማለት የሚያምኑ የቅብዓት ተከታይ ነበሩ፤ በኋላ ግን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሥጋ በተዋሕዶ ከበረ፤ የመወለድ ክብርም እንደ እኛ ተቀበለ በማለት የሚያምኑ ኾነዋል" ይላሉ። በአማን ነጸረ በሥርግው ሐብለ ሥላሴ አሳብ አለመስማማቱን የሚገልጠው፦

> የሥርግውን መደምደሚያ ለመቀበል ያስቸግራል። አንደኛ መምህር ኤስድሮስን አስቀድሞ ቅብዓት ነበሩ የሚሏቸው 'በመንፈስ ቅዱስ አዋሐጅነት ሰው ኾነ፣ መንፈስ ቅዱስ በማዋሐድ ቅብዓት ተባለ' ስላሉ ነው። ኾኖም ይህ አስተምህሮ በራሱ ቅብዓትን ገላጭ ነው ለማለት ያስቸግራል፤ አስተምህሮው ለተዋሕዶ እንጂ ለቅብዓት አይቀርብም። ሁለተኛ በካይላ ሜዳ ጉባኤ 'ተዋሕዶ' በሚል ስም የቀረበው አስተምህሮ 'በተዋሕዶ ወልድ ዋሕድ፤ በቅብዓት መሲሕ' የሚል የቀዳምያን ጻጎች አስተምህሮ ነውና። በቀደመ አቋማቸው መምህር ኤስድሮስ እንዲህ ስለማይሉ 'በቅብዓት መሲሕ' ማለትን ከካይላ ሜዳ ጉባኤ ቆርጦ 'ቀድሞ በተዋሕዶ ከበረ' ይሉ ነበረ መባሉ ትክክል ኾኖ አይታይም። ሦስተኛ ወደ ተጠቀሰው የጻጎች አስተምህሮ ማለትም 'በተዋሕዶ ወልድ ዋሕድ፣ በቅብዓት መሲሕ' ወደ ማለት የሔዱት በኋላ አቋማቸውን ቀይረው ነው። መምህር ኤስድሮስ ሃይማኖታቸውን ከተዋሕዶ ወደ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅነት ቀይረዋል። ይህም ባይኾን የታሪኩ ጸሐፊ አበጋዝ ዘሸዋ መፍቀሬ ጸጋ ስለ ነበሩ የሊቁን የዕውር[7] [ዐይነ ስውር] ኤስድሮስን ታሪክ ወደ ራሳቸው ስበውታል በማለት ነው (በአማን፣ ፳፻፲፪ ዓ.ም.)።

[7] በቀድሞ ጊዜ ዕውር ማለት የተለመደ ቢኾንም በአሁኑ ጊዜ ዐይነ ስውር በሚለው ቃል ተተክቷል።

“በመንፈስ ቅዱስ አዋሐጅነት ሰው ኾነ፤ መንፈስ ቅዱስ በማዋሐድ ቅብዐት ተባለ” የሚለው አስተምህሮ ከቅብዐት ይልቅ ለተዋሕዶ እንደሚቀርብ በአማን ነጸረ (፳፻፲፪) መግለጡን ልብ ይሏል። ይህ ገለጣ ለሊቃውንቱ እንጂ ላልተማረው ክርስቲያን ከባድ መኾኑ አያጠያይቅም። መምህር ኤስድሮስ በእርግጥ እንዲህ ብለው ያምኑ ወይም አያምኑ እንደ ነበረ በርግጠኛነት መናገር አይቻልም። በአማን ነጸረ አፍቃሬ ጸጋ የሚላቸው አበጋዝ ዘሸዋን በዋቢነት በመጥቀስ ነው። ይኹን እንጂ በጎንደር ዘመን በተጻፉ ዜና መዋዕሎች መምህር ኤስድሮስ አስቀድሞ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ብለው ያምኑ እንደ ነበር የሚገልጥ ማስረጃ አላገኘሁም። ተዋሕዶዎች የሚያምኑት “በግብረ መንፈስ ቅዱስ በተዋሕዶ ከበረ” ብለው ሲኾን ቅብዐቶች የሚያምኑት ደግሞ “ተዋሕዶ ምንታዌን[8] አጠፋ፤ ቅብዐት አከበረ” ብለው ነው። ከዚህ ላይ ለመጥቀስ የተፈለገው ጸሐፍያን ስለ ሊቁ ያላቸውን አስተያየት ለማሳየት በመኾኑ ከዚህ በላይ ማብራራት ከርእሰ ጉዳዩ መውጣት ነው።

የእኔ አሳብ የታሪኩ ጸሐፊ አበጋዝ ዘሸዋ መፍቀሬ ጸጋ ስለ ነበሩ የሊቁን የመምህር ኤስድሮስን ታሪክ ወደ ራሳቸው ስበውታል ወደ ሚለው ያደላል። ምክንያቱም ከቅዳሜ መስከረም ፳፪ ጀምሮ እሑድን ሳይጨምር እስከ ረቡዕ መስከረም ፳፮ ቀን ፲፯፻፶፮ ዓ.ም. ድረስ በካይላ ሜዳ በተካሄደው ጉባኤ ሊቁ መምህር ኤስድሮስ በመጀመሪያው ቀን አገር ለቀው እንዲሰደዱ፣ መስከረም ፳፮ ቀን በዕለተ ረቡዕ ደግሞ በደሴተ ምጽራሐ እንዲጋዙ ቅብዓቶች እና ጸጎች ተባብረው ራስ ወልደ ልዑልን መከታ አድርገው ዐዋጅ ያስነገሩባቸው የተዋሕዶ እምነት ተከታይ በመኾናቸው እንጂ የቅብዓት ተከታይ ስለ ኾኑ አልነበረም (ጊዩዲ፣ ገጽ ፪፻-፪፻፩)። ሊቁ የጸጋ አስተምህሮ ደጋፊ ቢኾኑ ኖሮ የመሰደድ ዕጣ አይገጥማቸውም ነበር ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም አሳዳጆቹ ቅብዓቶች እና ጸጎች ግንባር ፈጥረው ነበርና። ሥርግው (፲፱፻፹፩) ከቅብዓት ወደ ተዋሕዶ መመለሳቸውን የሚነግሩን የመምህር ኤስድሮስን ብቻ ሳይኾን እርሳቸው ደቀ መዝሙራቸው ነበሩ የሚሏቸውን የሊቁን የአራት ዓይና ጎሹን ጭምር ነው። ነገር ግን አራት ዓይና ጎሹ የመምህር ኤስድሮስ ተማሪ አልነበሩም፤ ሁለቱ ሊቃውንት በነበሩበት ዘመን መካከል ቢያንስ የዘጠና ዓመት ልዩነት ነበረ።

[8] ምንታዌ ሁለትነት ማለት ነው። ቃሉ አገልግሎት ላይ የሚውለው በነገረ ክርስቶስ አስተምህሮ ላይ ነው። ተዋሕዶ ምንታዌን አጠፋ ማለት ሁለትነትን አጠፋ ማለት ነው። አጠፋ የሚባለውም በተዐቅቦ እንጂ በመጠፋፋት አለመኾኑን መረዳት ይገባል።

## ፰. መምህር ኤስድሮስ የነበሩበት ዘመን በሊቃውንቱ እይታ

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (፲፱፻፹፩) "የመምህር ኤስድሮስን አስተምህሮ ደቀ መዝሙራቸው አራት ዓይና ጎሹ ቀጠሉበት" በማለት የጻፉት በሁለት ምክንያት ማስተካከያ የሚፈልግ ይመስለኛል። የመጀመሪያው በካይላ ሜዳ ጉባኤ "በተዋሕዶ ከበረ" ብለው የሚያምኑ በመኾናቸው ተወግዘው ወደ ምጽራሐ ደሴት እንዲጋዙ ዐዋጅ ተነግሮባቸው የነበሩትን ሰው ቅብዓት እንደ ነበሩ መጻፋቸው ትክክል ባለ መኾኑ ነው። ሁለተኛው ስሕተት ደግሞ አራት ዓይና ጎሹን የመምህር ኤስድሮስ ተማሪ አድርገው መግለጣቸው ነው። መምህር ኤስድሮስ ያረፉበት ዘመን ባይጠቀስም ተማሪያቸው ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ እንኳ ያረፉት ከ፴፪ ዓመታት አገልግሎት በኋላ ጥቅምት ፲፯፻፺፬ ዓ.ም. ነው። እስከ አሁን ካቀረብናቸው የምሁራን ጽሑፎች መረዳት የሚቻለው ከሰኔ ፲፣ ፲፯፻፸፫ ዓ.ም. በኋላ ስለ ሊቁ ስለ መምህር ኤስድሮስ የሚገልጡ ማስረጃዎች አለመገኘታቸውን ነው። በተጠቀሰው ዘመን መምህር ኤስድሮስ በዕድሜ መግፋት ምክንያት ሊደክሙ ቢችሉ እንኳን ቅባቶችና ጸጎች ግንባር ፈጥረው በጎንደር እንዲኖሩ ስላልፈቀዱላቸው ለስደት መዳረጋቸውን መረዳት ይገባል።

አራት ዓይና ጎሹ የተወለዱት መምህር ኤስድሮስ ካረፉ በኋላ በ፲፯፻፹፩ ዓ.ም. አካባቢ መኾኑ ነው። እንደ ብርሃኑ ድንቄ ገለጣ ከኾነ ደግሞ የአራት ዓይና ጎሹ ልደት ከዚህም በኋላ መኾኑን መረዳት ይቻላል። አራት ዓይና ጎሹ ያረፉት በ፹ ዓመታቸው ነው የሚሉትን ወገኖች አሳብ ብንቀበል እንኳ ሊቁ ሊወለዱ የሚችሉት በ፲፯፻፹፩ ዓ.ም. አካባቢ ይኾናል። ምክንያቱም ጌታቸው ኃይሌ (፳፻፰) እንደሚሉት ሊቁ አራት ዓይና ጎሹ ያረፉት ጥር ፳፪ ቀን ፲፰፻፷፩ ዓ.ም. ሲኾን ሊቁ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጆምበሬ (፳፻፲፪) እንደ ጻፉት ደግሞ ጥር ፳፱ ቀን ፲፰፻፷፩ ዓ.ም. ነው። አራት ዓይና ጎሹ በዚህ ዓለም ፷፫ ዓመት መኖራቸውን የሚጠቅሱትን ሊቃውንት አሳብ ከተቀበልን ደግሞ ሊቁ ሊወለዱ የሚችሉት በ፲፯፻፺፰ ዓ.ም. አካባቢ ስለሚኾን መምህር ኤስድሮስ አስተማሯቸው የሚለው ትክክል አይኾንም። እንኳን እርሳቸውን መምህራቸውን አቶ አደራህንም መምህር ኤስድሮስ አላስተማሯቸውም። ይህን አስመልክቶ ቀሲስ ዶክተር አምሳሉ ተፈራ (፳፻፲፩) የመምህራንን ሐረገ ትውልድ ሲያስረዱ መምህር ኢስድሮስን ለአቶ አደራህ ዐምስተኛ ትውልድ ሲያደርጓቸው፣ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ (ኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ፣ ፳፻) ደግሞ የአቶ አደራህ ዐራተኛ ትውልድ ያደርጓቸዋል። ይህም አቶ አደራህ መመህር ኤስድሮስን አላስተማሯቸውም የሚለውን የሚያጠንክር ይኾናል።

> ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ካረፉ ከብዙ ዓመታት በኋላ የተወለዱት አራት ዓይና ጎሹ ለመምህር ኤስድሮስ ደቀመዝሙር ሊኾኑ አይችሉም። የአራት ዓይና ጎሹ መምህርም አቶ አደራህ እንጂ መምህር ኤስድሮስ አለ መኾናቸውን

መረዳት ያስፈልጋል። "መምህር ኤስድሮስ ይህን ሁሉ ካገለገሉ በኋላ በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ዐርፈዋል" ተብሎ በዳንኤል ክብረት የተጻፈውም (፳፻፲፪) እንዲሁ እርማት የሚያስፈልገው ነው። ምክንያቱም ሊቁን መምህር ኤስድሮስን የተኳቸው ደቀ መዝሙራቸው ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ እንኳ ያረፉት በ፲፯፻፺፬ ዓ.ም. ነው። ከዐቃቤ ሰዓት ከብቴ በመቀጠል መምህር ወልደ አብ ወንበር ተክለው ሲያስተምሩ ኖረው ያረፉት በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን መኾኑን አለቃ ይኵኖ አምላክ ነግረውናል (ይኵኖ አምላክ፣ ፲፱፻፶፰)። ይህን የምለው ወልደ አብ ከመምህር ኤስድሮስ ሦስተኛ ትውልድ መኾናቸውን የገለጡትን ጸሐፊዎች አሳብ ሳላካትት ነው። እርሱን ባካትት ልዩነቱ ይሰፋል እንጂ አይጠብም። እንደ ቴዎድሮስ አብርሃ (ኢ. አ፣ ቅጽ ፪፣ ገጽ ፬፻፸፫) ከኾነ ደግሞ አራተኛ ትውልድ መኾናቸው ነው።

መምህር ኤስድሮስ ካይላ ሜዳ በተደረገው ጉባኤ እንዲጋዙ የተፈረደባቸው ዐፄ ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው ከዘጠና ዓመት በፊት በመኾኑ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን አልደረሱም። አለቃ ይኵኖ አምላክ በ፲፰፻፵፫ ዓ.ም. አርፈዋል ብለው የገለጡት መምህር ኤስድሮስን ሳይኾን ሊቁ በትምህርት የወለዷቸው የተማሪያቸው (የስመ ክርስቶስ) ደቀ መዝሙር (የልጅ ልጃቸው/የደቀ መዝሙራቸው ደቀ መዝሙር) የነበሩትን መምህር ወልደ አብን ነው። እዚህ ላይ ግልጥ ማድረግ የሚገባው ወልደ አብ ከሸዋ ወደ ጎንደር የገቡት፣ መምህር ኤስድሮስ አንድም በድካም ካለዚያም ጸጎች ባደረሱባቸው ጫና ምክንያት ጎንደርን በለቀቁበት በ፲፯፻፸፩ ዓ.ም. አካባቢ በመኾኑ አራት ዐይና ጎሹ ደቀ መዝሙራቸው የነበሩት የሥነ ክርስቶስ እንጂ የመምህር ኤስድሮስ ተማሪ ያልነበሩ መኾኑን ነው። በተጨማሪም ወልደ አብ በዚህ ዘመን አካባቢ ጎንደር መግባታቸውን አሻግሬ አምጤ (፳፻፲፫፣ ገጽ ፻፲፯፣ ያልታተመ) እና እና መንክር መኮንን (፲፱፻፸፪፣ ገጽ ፳፪) ገልጸዋል።

መምህር ኤስድሮስ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን አልደረሱም፤ ዘመነ መሳፍንት ሲጀምር በሕይወት የነበሩት ደቀ መዝሙራቸው ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ እንጂ እርሳቸው አይደሉም። በ፲፯ኛው ምእት መጨረሻ አጋማሽ የተወለዱት እና ከሰኔ ፲ ቀን ፲፯፻፸፫ ዓ.ም. በኋላ ስለ እርሳቸው በሕይወት መኖር የሚገልጥ ምንም መረጃ የማይገኝላቸውን መምህር ኤስድሮስን በ፲፰፻፵፯ ዓ.ም. በነገሡት በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን ዐረፉ ማለት ምክንያታዊ አይኾንም። ሥርግው ሐብለ ሥላሴም መምህር ኤስድሮስ አራት ዓይና ጎሹን ማስተማራቸውን ስለ ነገሩን በቀጥታ ከቴዎድሮስ ዘመን ደረሱ ባይሉ እንኳ መቃረባቸውን እየጠቆሙን ነው። የዳንኤል ክብረትም፣ የሥርግው ሐብለ ሥላሴም አሳብ ማስተካከያ ይፈልጋል የምለው አባቶቻችን ወንበር ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ በኋላ ከመቶ ዓመታት በላይ መኖራቸውን በመጠራጠር ሳይኾን የተጻፈ የታሪክ ማስረጃ ባለማግኘቴ ነው።

## ፱. ማጠቃለያ

“የመምህር ኤስድሮስ የሕይወት ታሪክ እና አበርክቷቸው” በሚል ርእስ የተዘጋጀው ይህ ጥናት ሊቁ በድሮው ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ተወልደው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በዚያው በትውልድ አካባቢያቸው መማራቸውን ያስነብበናል። ሊቁ በትግራይ ዜማ ከተማሩ በኋላ በዘመኑ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ወደ ነበረችው ወደ ጎንደር ሄደው ቅኔን፣ መጻሕፍተ ብሉያትን፣ መጻሕፍተ ሐዲሳትን፣ መጻሕፍተ መነኮሳትን እና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ተምረው በማጠናቀቃቸው አራት ዓይና ከመባል ደረጃ መድረሳቸውን ይነግረናል።

ሊቁ መምህር ኤስድሮስ ይህን ሁሉ ዕውቀት ተምረው በመምህርነት ተመርቀው ወንበር ዘርግተው ማስተማር ቢጀምሩም የጥንቱ “የላይ ቤት” ትርጓሜ ውስብስብ በመኾኑ ለመረዳት ብዙ ጊዜ የሚጠይቅ መኾኑ ዕረፍት አልሰጣቸውም። በመኾኑም ወንወበራቸውን አጥፈው እንደ ገና ጣና ሐይቅ ውስጥ ወደሚገኙ ገዳማት በመሄድ ከሦስት መቶ በላይ መጻሕፍት አስነብበው የጥንቱንም መርምረው ለተማሪዎቻቸው ቀላል በኾነ መንገድ መግለጥ የሚችሉበትን ስልት ነድፈው “የታች ቤት” የሚባለውን የትርጓሜ ስልት አዘጋጁ። የሚያስገርመው ሊቁ የረቀቀ ዕውቀት የነበራቸው ቢኾንም፣ የሰበሰብኩት ዕውቀት ይበቃኛል ብለው ሳይመኩ፣ ደቀ መዝሙሮቻቸውን ዳግም ጠርተው በአእምሯቸው የቀረጹትን ዐዲሱን ስልት ተቀበሉ ከማለት ይልቅ ከሊቃውንቱ (ከተማሪዎቻቸው) ጋር እየተወያዩ በማርቀቅ የተስማሙበት ተጽፎ ማስተማሪያ እንዲኾን ማድረጋቸው ለዚህ ትውልድ አርአያ የሚኾን ነው።

መምህር ኤስድሮስ ለደቀ መዝሙሮቻቸው ያደረጉት ዳግም ጥሪ በሁሉም ደቀ መዝሙሮቻቸው ተቀባይነት አለማግኘቱን ከታሪካቸው የምንረዳው ነው። ጥሪውን ሳይቀበሉ የቀሩት የጥንቱን ትርጓሜ ይዘው ሲቀጥሉ ወደ መምህራቸው የሄዱት ደግሞ ዐዲሱን ትርጓሜ መከተላቸውን ይህም ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሁለት ትርጓሜ ስልቶች ባለቤት እንዳደረጋት ከጽሑፉ እንረዳለን። መምህር ኤስድሮስ በተዋሕዶ ከበረ ብለው ያምኑ ስለ ነበረ አፍቃሬ ቅብዓት በነበሩ እና ሦስት ልደት የጸጋ ልጅነት ብለው በሚያምኑ የጎንደር ነገሥታት ሲሳደዱ መኖራቸውን ከጥናቱ እንረዳለን። ከ፲፯፻፸፭ ዓ.ም. በኋላ ስለ ሊቁ አለመታወቁ ያረፉበትን ቦታ በአስተማማኝ ማስረጃ እንዳንገነዘብ እንዳደረገን ጽሑፉን ስናነብ የምናረጋግጠው እውነታ ሲኾን በሊቁ ሕይወት እና አበርክቶ ዙሪያ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች ጥሩ መነሻ ሊኾናቸው ይችላል።

## ዋቢ መጻሕፍት

ሀብተ ማርያም ወርቅነህ። (፲፱፻፷፪)። *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።

መርስዔ ኅዘን ወልደ ቂርቆስ። (፲፱፻፶፯)። *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ*። ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

መንክር መኮንን። (ጥር ፲፱፻፹፪)። *መጽሔተ ሊቃውንት*። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት።

መንክር መኮንን። (ጥር ፳፻፲፬)። *መጽሔተ ሊቃውንት*። ከኑ ማተሚያ ቤት።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። (፲፱፻፹፰)። *የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*። ቅጽ ፫።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። (፲፱፻፺፮)። *የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት*። ቅጽ 7።

በአማን ነጸረ። (፳፻፲፪)። *ጽንዐ ተዋሕዶ*። ጃጃው አታሚዎች።

ተሾመ ዘሪሁን (መልአከ ታቦር)። (፳፻፱)። *ዝክረ ነገር*። ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ. የግ.ማኅበር።

ጎሩይ ወልደ ሥላሴ። (፲፱፻፳፫)። *የሕይወት ታሪክ።* ብርሃንና ሰላማ ማተሚያ ቤት።

አምሳሉ ተፈራ። (፳፻፲፮)። *ነቅዐ መጻሕፍት*። ጃጃው አታሚዎች።

አሻግሬ አምጤ። (፳፻፲፫)። *ፍኖተ ሊቃውንት*። (በኅትመት ላይ ያለ)።

አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ። (መጋቢት ፲፱፻፵፫)። *መርሐ ልቡና።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ። (፲፱፻፵፯)። *መጽሔተ አሚን።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት።

አድማሱ ጀምበሬ። (፳፻፲፪)። *መጽሐፈ ቅኔ (ዝክረ ሊቃውንት*) ፩ኛ ዕትም። ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት ።

ዓምደ ጽዮን ተሰማ (አለቃ)። (መስከረም፣ ፲፱፻፹፪) *ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ መምህር ኤስድሮስ።* ትንሣኤ መጽሔት፣ ቁጥር ፳፩፣ ገጽ ፲፱-፳።

ከፍያለው መራሔ። (፳፻፫)። *ዝክረ ሊቃውንት*። (ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ)

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ ክ/። (፲፱፻፺፪)። *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ድርጅት።

የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/:: (፳፻):: *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ ፳፻*:: ሜጋ አታሚዎች ፒኤል ሲ::

የእስቴ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሕንጻ ዕድሳት ኮሚቴ:: *ዝክረ ደብረ ሃይማኖት መካነ ኢየሱስ*:: ማተሚያ ቤቱ ያልታወቀ::

ይኵኖ አምላክ (አለቃ):: ():: *የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜያቸው::* Journal of Ethiopian Studies, 4(1), ፸፫-፻፲፱::

ደምፀ አንበርብር:: (፳፻፮):: *ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጓሜ*:: ማተሚያ ቤቱ ያልታወቀ::

ዳንኤል ክብረት:: (፳፻፲፪):: *የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች*:: ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት አገልግሎት::

ጌታቸው ኃይሌ:: (፳፻፮):: *ባሕረ ሐሳብ*:: ማተሚያ ቤቱ ያልታወቀ::

Blundell, W. H. (1922). The *Royal Chronicle of Abyssinia* 1769-1840. Cambridge Univerisity Press.

*COWLEY, R. W.* (1974). Old Testament Introduction in the Andemta commentary tradition. *Journal of Ethiopian Studies,* 12(1), 133–175. http://www.jstor.org/stable/44324703

Guidi, ignazio. (1910). *Annales Regum Iyasu II Iyo'as et Bekaff*. Parisiis: E. typographeo reipublicae

Tedros Abraha. (2005). Exegesis. In Ulig, S. (2005) Encyclopedia Aethiopica. Harrassowitz Verlag